


በፕሬዘደንት ቶማስ ኤስ ሞንሰን

# ታዛዥነት በረከቶችን ያመጣል

***የእውነት እውቀት እና ለታላቅ ጥያቄዎቻችን መልሶች የሚመጡት ለእግዚአብሔር ትእዛዛት ታዛዥ ስንሆን ነው።***

ውድ ወንድሞቼና እህቶቼ፣ በዚህ ጠዋት ከእናንተ ጋር በመሆኔ ታላቅ ምስጋና ይሰማኛል። እናንተን ለማነጋገር ያለኝን እድል ስጠቀም የእናንተን እምነትና ጸሎት እጠይቃለሁ።

በዘመናት በሙሉ፣ ወንዶችና ሴቶች ስለዚህ ስጋዊ ህይወት እና በዚህ ቦታ ስላላቸው ሀላፊነትና ስለዚህ ህይወት አላማ፣ እንዲሁም ሰላምና ደስታ ስለሚያገኙበት መንገድ እውቀትና መረጃ ለማግኘት ፈልገዋል። እንደዚህ አይነት ፍለጋ በእያንዳንዳችን ይደረጋል።

ይህ እውቀት እና መረጃ ለሰው ዘር በሙሉ የሚገኝ ነው። ዘለአለማዊ በሆኑ እውነቶች ውስጥ የተያዙ ናቸው። በትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ክፍል 1 ቁጥር 39 እንደምናነበው፣ “ስለሆነም፣ እናም አስተውሉ፣ ጌታ አምላክ ነው፣ መንፈስም ይመሰክራል፣ እናም ምስክርነቱም እውነት ነው፣ እናም እውነት ከዘለአለም እስከ ዘለአለም ይኖራል።

ገጣሚው እንደጻፈው

*ሰማዮች ቢሄዱም እና የምድር መንጮች ቢፈነዱም*
*የኑሮ ጠቅላላ ድምር የሆነው እውነት እጅግ የከፋውንም ይቋቋማል፣*
*ለዘለአለም፣ ዘለአለማዊ፣ የማይቀየር ነውና።*[1]

አንዳንዶች፣ “እንደዚህ አይነት እውነት የት ነው የሚገኘው፣ እናም እንዴት ነው የምናውቀው?” ብለው ይጠይቃሉ። በከርትላንድ ኦሀዩ ፣ በግንቦት 1833 (እ.አ.አ) በነብዩ ጆሴፍ ስሚዝ በኩል በተጸጠው ራእይ ውስጥ፣ ጌታ እንዲህ አወጀ፥

“እውነት ነገሮች እንዳሉ፣ እና እንደነበሩ፣ እና ወደፊት እንደሚሆኑ ማወቅ ነው። . . .

“የእውነት መንፈስም እግዚአብሔር ነው። . . .

“እና ትእዛዛቱን ካላከበሩ በስተቀር ማንም ሰው ሙላትን አይቀበልም።

“ትእዛዛቱን የሚያከብርም፣ በእውነት እና በሁሉም ነገሮች እውቀት እስከሚከበር ያክል፣ እውነት እና ብርሀንን ይቀበላል።”[2]

እንዴት የሚያስገርም ቃል ኪዳን ነው! “ትእዛዛቱን የሚያከብርም፣ በእውነት እና በሁሉም ነገሮች እውቀት እስከሚከበር ያክል፣ እውነት እና ብርሀንን ይቀበላል።”

ሙሉ ወንጌል ዳግም በተመለሰበት በዚህ በተብራራ ዘመን እኔና እናንተ ካርታ ባልተሰራለት ባህር ወይም ምልክት በሌለው መንገድ እውነትን የምንፈልግበት ምንም ምክንያት የለም። ወዳጅ የሰማይ አባት መንገዱን በአላማ ሰርቶልናል እናም የማይወቅብንን ካርታ—*ታዛዥነት ሰጥቶናል!*የእውነት እውቀት እና ለታላቁ ጥያቄዎቻችን መልሶች የሚመጡት ለእግዚአብሔር ትእዛዛት ታዛዥ ስንሆን ነው።

በህይወታችን በሙሉ ታዛዥነትን እንማራለን። ከልጅነታችን ጀምሮ፣ እኛን የሚንከባከቡ ደህንነታችንን ለማረጋገጥ መመሪያዎችንና ህግጋትን ይሰጡናል። እንደዚህ አይነት ህግጋትን ብናከብር ህይወት ለሁላችንም ቀላል ይሆናል። ብዙዎቻችን ግን የታዣዝነትን ጥቅም በአጋጣሚዎችን እንማራለን።

በልጅነቴ፣ በየበጋው ከሐምሌ እስከ መስከረም ቤተሰቤ በፕሮቮ ሸልቆ ውስጥ በሚገኘውው ቪቭያን ፓርክ በሸርሸር ቤታችን ውስጥ፡ እንቆይ ነበር።

በእነዚይ ችግር በሌለብን ቀናት ከልብ ጓደኞዎቼ አንዱ፣ ቤተሰቡ የሽርሽር ቤት በቪቭያን ፓርክ የነበራቸው፣ ዳኒ ላርሰን ነበር። በየቀኑ እርሱ እና እኔ ልጆች ንዙ ነገር ለማድረግ የሚችሉበትን ይህን ቦታ አሳ በማጥመድ፣ ድንጋዮችንና ሌሎች ውድ ነገሮችን በመሰብሰብ እና ኮረባታዎች ላይ በመውጣት፣ እና የየቀኗን እያንዳንድ ደቂቃና ሰዓት በመደሰት እንዞርበት ነበር።

አንድ ጠዋት ዳኒና እኔ ከሌሎቹ ጓደኞቻችን ጋር እሳት እያነደድን ለመጫወት ወሰንን። በቅርብ ባለው ሜዳ ላይ ቦታ የምንሰበስብበትን ቦታ ማዘጋጀት ነበረብን። በሳር የተሸፈነው ሜዳ የደረቀና እሾህማ ሆኖ አላማ ለነበረን አላማ የሚጠቅም አልነበረም። ትልቅ ክብ የሆነ ቦታን ለማዘጋጀት በማቀድ፣ ረጅም የሆኑትን ሳሮች ማጨድ ጀመርን። በሀይላችን በሙሉ ሳሩን መሳብ ጀመርን፣ ነገር ግን ለማጨድ የቻልነው ትንሽ አስቸጋሪ አረሞችን ብቻ ነበር። ይህ ስራ ሙሉ ቀን የሚፈጅ እንደሆነ አውቀን ነበር፣ እናም ሀይላችን እና ፍላጎታችን እየቀነሰ መጣ።

ከዚያም ለዚህ ጥሩ መፍትሄ እንደሆነ የመሰለኝ ሀሳብ ወደ ስምንት አመት አዕምሮዬ መጣልኝ። ለዳኒም እንዲህ አልኩት፣ “ማድረግ ያለብን አረሙን በእሳት ማያያዝ ነው። በሜዳው ሳር ክብ የሆነ ቦታ *ብቻ እናነዳለን!”* እርሱም ወዲያ ባልኩት ተስማማ፣ እናም ክብሪቶች ለማምጣት ወደ ሽርሽር ቤታችን ሮጬ ሄድኩኝ።

በስምንት አመቴ ክብሪት ለመጠቀም ፈቃድ እንደነበረኝ እንዳታስቡ፣ ዳኒ እና እኔ

እነዚህን ያለመቆጣጠሪያ ለመጠቀም ፈቃድ አንዳልነበረን ግልጽ ለማድረግ እፈልጋለሁ። ሁለታችንም ስለእሳት አደጋ በተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶን ነበር። ነገር ግን፣ ቤተሰቦቼ ክብሪቶችን የት እንደሚያስቀምጡ አውቅ ነበር፣ እናም ሜዳዎችን ማጽዳት ያስፈልገን ነበር። ሌላ ሀሳብ በአዕምሮዬ ሳይገባ፣ ወደ ሽርሽር ቤታችን ሮጥኩኝ እናም ሌሎች እንደማያዩኝ በማረጋገጥ ክብሪቶችን ወሰድኩኝ። ቶሎ በአንደኛው ኪሴ ውስጥ ደበቅኳቸው።

ለችግራችን መፍትሄ በኪሴ ስላለኝ በመደሰት፣ ወደ ዳኒ በመሮጥ ተመለስኩኝ። እሳቱ እስከምንፈልገው ቦታ ድረስ ነድዶ ራሱን እንደሚያጠፋ አስብ እንደነበር አስታውሳለሁ።

ክብሪቱን ጫርኩኝ እና የደረቀውን ሳር አነደድኩት። በጋዝ እንደተተነከረ አይነት በእሳት ወዲያው ተያዘ። በመጀመሪያ ዳኒ እና እኔ ሳሩ ሲነድ በደቀት ተመለከተው፣ ነገር ግን እሳቱ በብቻው ሊጠፋ እንደማይችል አወቅን። ይህን ለማጥፋት እንደማንችል ስናውቅ፣ ደነገጥን። እሳቱም ሳሩን እያነደደ ዛፎችንና ከዚያ በኋላ ያሉትን በአደጋ ላይ እያደረሰ ወደ ተራራው ተጓዘ።

በመጨረሻም ለእርዳታ ከመሮጥ ሌላ ምንም ምርጫ አልነበረንም። ወዲያም በሽቪያን ፓርክ የነበሩት ሰዎች በሙሉ ውሀ በተነከረ አልጋ ልብሶች እሳቱን በመደብደብ ብለማጥፋት መሯሯጥ ጀመሩ። ከብዙ ሰዓት በኋላ ቀሪው የእሳቱ ፍሞች ጠፉ። ብዙ እድሜ የነበራቸው ዛፎች እና እሳቱ ይደርስባቸው የነበሩ ቤቶች ሁሉ ዳኑ።

ዳኔ እና እኔ በዚያ ቀን አስቸጋሪ ቢሆንም አስፈላጊ የሆነ ትምህርትን ተማርን -- ከእነዚህ ታላቅ የነበረውም የታዛዥነት አስፈላጊነት ነበር።

የሰውነት ደህንነታችንን የሚጠብቁ ህግጋት አሉ። እንደዚህም፣ አስቸጋሪ የሆነውን ይህን ስጋዊ ህይወት በውጤታማነት ለመጓዝ እና በመጨረሻም ወደ ሰማይ አባታችን ለመመለስ እንድንችል ዘንድ ጌታ የመንፈስ ደህንነታችንን የሚያረጋግጡ መመሪያዎችና ትእዛዛት ሰጥቶናል።

ከመቶ አመቶች በፊት፣ በእንሥሣት መስዋዕት የማድረግ ባህል ለነበራቸው ትውልዶች፣ ሳሙኤል እንዲህ በድፍር አወጀ፥ “መታዘዝ ከመሥዋዕት፥ ማዳመጥም የአውራ በግ ስብ ከማቅረብ ይበልጣል።”[3]

በዚህ ዘመንም፣ ጌታ “ልብን እና መልካም ፈቃድ ያለውን አዕምሮ ይሻል፤ እናም ፈቃድ ያለው እና ታዛዥ የሆነው እርሱ በእነዚህ በመጨረሻዎቹ ቀናት የፅዮንን ምድርን በረከት ይበላሉ” በማለት ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ገልጾ ነበር።[4]

የጥንት እና የአሁን ዘመን ነቢያት በሙሉ ታዛዥነት ለደህንነታችን አስፈላጊ እንደሆነ ያውቁ ነበር። ኔፊ “ጌታ ያዘዘኝንም ነገሮች አደርጋለሁ።”5 ስለኔፊ እንዳወጀው፣ “እሄዳለሁ፣ ጌታ ያዘዘኝንም ነገሮች አደርጋለሁ።”[5]ሌሎች በእምነታቸውና በታዛዥነታቸው ቢደናቀፉም፣ ኔፊ አንዴም ቢሆን ጌታ እንዲያደርቅ የጠየቀውን ባለማከናወን አልወደቀም። በዚህም ምክንያት ለመቆጠር የምይችሉ ትውልዶች ተባርከዋል።

ነፍስን የሚያነሳሳ የታዛዥነት ታሪክ የአብርሀምና የይስሀቅ ታሪክ ነው። አብርሀም ታዛዥ በመሆን፣ ውድ ልጁን ይስሀቅን ወደ ሞሪያም ምድር በመሄድ እርሱን እንደ መስዋዕት እንዲያቀርብ በጌታ የታዘዘበትን ማክረቡ እንዴት አስቸጋሪ ይሆንበት ነበር። ወደ ተመደበብት ቦታ ሲጓዝ አብርሀም ያለው ሀዘን ምን እንደሆን ይሰማችኋልን? ይስሀቅን አስሮ፣ በመሰዊያው ላይ ሲያስተኛው፣ እናም እርሱን ለመግደል ቢላዋውን በእጁ ሲይዝ፣ ሀዘኑ ሰውነቱንና አዕምሮውን አስጨንቀዋቸው እንደነበር እርግጥ ነው። በማይወላወል እምነት እና በጌታ በፍጹም በማመን፣ የጌታን ትእዛዝ አከበረ። እንዲህ የሚለው ጥሪ እንዴት አስደናቂ ነበር ፣ እና በምን በሚያስገርም ሁኔታ መጣ፥ “በብላቴናው ላይ እጅህን አትዘርጋ፥ አንዳችም አታድርግበት፤ አንድ ልጅህን ለእኔ አልከለከልህምና እግዚአብሔርን የምትፈራ እንደ ሆንህ አሁን አውቄአለሁ።”[6]

አብርሀም ተፈትኖና ተሞክሮ ነበር፣ እናም ለታማኝነቱና ለታዛዥነቱ ጌታ ይህን ግርማዊ ቃል ኪዳን ሰጠው፥ “የምድር አሕዛብ ሁሉም በዘርህ ይባረካሉ፥ ቃሌን ሰምተሃልና።”[7]

ምንም እንኳን ታዛዥነታችንን በእንደዚህ አይነት አስገራሚና ልብ በሚሰብ መንገድ እንድናረጋግጥ ባንጠየቅም፣ ታዛዥነት ከሁላችንም የሚጠበቅብን ነው።

ፕሬዘደንት ጆሴፍ ኤፍ. ስሚዝ በጥቅምት 1873 (እ.አ.አ) እንዳወጁት፣ “ታዛዥነት የሰማይ የመጀመሪያ ህግ ነው።”[8]

ፕሬዘደንት ጎርደን ቢ. ሒንክሊ እንዳሉት፣ “የኋለኛው ቀን ቅዱሳን ደስታ፣ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን ሰላም፣ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን እድገት፣ እና የዚህ ህዝብ ዘለአለማዊ ደህንነትና ዘለአለማዊነት የሚገኘው በእግዚአብሔርን ምክሮች ታዛዥ በመሆን ነው።”[9]

ታዛዥነት የነቢያት ልምድ ጸባይ ነው፤ በዘመናት በሙሉ ይህ ለእነርሱ ጥንካሬና እውቀት ሰጥቷል። እኛም ለዚህ ጥንካሬና እውቀት ምንጭ መብት እንዳለን መረጋታችን አስፈላጊ ነው። ይህም የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ስናከብር በቀላል እያንዳንዳችን ልናገኘው የምንችል ነው።

በአመታት ሁሉ በልዩ ታማኝና ታዛዥ የሆኑ ለመቁጠር የማይቻሉ ሰዎችን አውቃለሁ። በእነርሱ ተባርኬአለሁ እናም ተነሳስቻለሁ። ከእነዚህ ስለሁለቱ ሰዎች ላካፍላችሁ።

ዋልተር ክራውስ ቤተሰብ ያለው፣ ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በኋላ እንደ ምስራቅ ጀርመን በሚባለው ውስጥ የሚኖር የቤተክርስቲያና ታማኝ አባል ነበር። በነበረበት የአለም ክፍል ነጻነት ስላልነበረ ችግር ቢኖርበትም፣ ወንድም ክራውስ ጌታን የሚወድና የሚያገለግል ሰው ነበር። በታማኝነት እና በጥንቃቄ የተሰጡትን እያንዳንዱን ሀላፊነቶች ያሟላ ነበር።

ሌላው ሰውም፣ በ1911 (እ.አ.አ) በ17 አመቱ በጀርመኒ ውስጥ ተቀይሮ የተጠመቀ በሀጋሪ የተወለደ ሰው ነበር። ወዲያውም ወደ ሀንጋሪ ተመለሰ። ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በኋላ በድብረሰን ከተማ ውስጥ እንደ እስረኛ ይኖር ነበር። በሀንጋሪም ነጻነት ተወስዶባቸው ነበር።

ወንድም ደንዶርፈርን የማያውቀው ወንድም ዋልተር ክራውስ የእርሱ የቤት ለቤት አስተማሪ እንዲሆንና በየጊዜው እንዲጎበኘው ሀላፊነት ተሰጠው። ወንድም ክራውስ አብሮ የሚያስተምረውን ጓደኛ ጠርቶ እንዲህ አለው፣ “ወንድም ዮሀም ደንዶርፈርን እንድንጎበኝ ሀላፊነት ተቀብለናል። ከእኔ ጋር በዚህ ሳምንት እርሱን ለመጎብኘት እና የወንጌል መልእክት ትችላለህን?” እና ከዚያም “ወንድም ደንዶርፈር የሚኖረው በሀንገሪ ውስጥ፡ ነው” አለው።

የደነገጠው የአገልግሎት ጓደኛውም “መቼ ነው የምንሄደው?” በማለት ጠየቀ።

ወንድም ክላውስም “ነገ” ብሎ መለሰ።

“መቼ ወደ ቤት እንመለሳለን?” ብሎ ጋደኛው ጠየቀ።

ወንድም ክላውስም፣ “ምናልባት ከሳምንት በኋላ፣ —ከተመለስንም” በማለት መለሰ።

ሁለቱ አስተማሪዎች ወንድም ደንዶርፈርን ለመጎብኘት ረጅም ጉዞ በነበረው በባቡርና በአውቶቡስ ሄዱ። ወንድም ደንዶርፈር የቤት ለቤት አስተማሪዎች ከጦርነቱ በፊት ጀምሮ አልነበራቸው። አሁን፣ እነዚህን ሁለት የጌታ አገልጋዮች ሲመለከት፣ እነርሱ በመምጣታቸው የነበረው ደስታ ታላቅ ነበር። በመጀመሪያ የእነርሱን እጅ ለመጨበት እምቢ አለ። እና ወደ መኝታው ሄዶ ለብዙ አመት ያጠራቀማቸውን አስራት አመጣ። የቤት ለቤት አስተማሪዎቹም ገንዘቡን ሰጠ እናም “አሁን ለጌታ ያለኝን ሀላፊነት አከናውኛለሁ። አሁን የጌታ አገልጋዮችን እጆች ለመጨበት ብቁነት ይሰማኛል” አለ። ይህ ከቤተክርስቲያና ጋር ለብዙ አመት ግንኙነት ያልነበረው ታማኝ ወንድም

ከነበረው ትንዝ ገቢ አስራቱን የሚከፍልበትን ማጠራቀሙ በጣም ቃላት በሌለው መንገድ እንዳስደነቀው ወንድም ክራውስ ነግረውኝ ነበር። ይህን መቼ ለመክፈል እንደሚችል ሳያውቅ ነበር ያጠራቀማቸው።

ወንድም ዋልተር ክራውስ በ94 አመታቸው ከዘጠኝ አመት በፊት ሞቱ። በህይወታቸው በሙሉ በታማኝነትና በታዛዥነት አገለገሉ እናም ለእኔና ለሚያውቋቸው በሙሉ የሚ ያነሳሱ ነበሩ። ሀላፊነት ሲሰጣቸው፣ ምንም አይጠይቁም፣ አያጉረመርሙም፣ እናም ለማድረግ የማይችሉበትን ምክንያት በምንም አይሰጡም ነበር።

ወንድሞቼና እህቶቼ፣ የህይወት ታላቅ ፈተና ታዛዥነት ነው። ጌታ እንዳለው፣ "ጌታ አምላክ የሚያዛቸውን ማናቸውንም ነገሮች ሁሉ እንደሚያደርጉ ለማየት፣ በዚህ እንፈትናቸዋለን።"[10]

አዳኝ እንዳወጀውም፥ "ከእጁ በረከት የሚያገኙም ለዚያ በረከት የተመደበውን ህግና አለም ከመመስረቷም በፊት በስራ ላይ የዋሉትን ቅድመ ሁኔታ ሊኖሩባቸው ያስፈልጋቸዋልና።"[11]

ከአዳኝ በላይ የሆነ የታዛዥነት ምሳሌ የለም። ስለእርሱም ጳውሎስ እንዳስመለከተው፥

"ምንም ልጅ ቢሆን፥ ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ፤

"ከተፈጸመም በኋላ . . .ለሚታዘዙለት ሁሉ የዘላለም መዳን ምክንያት ሆነላቸው።"[12]

ፍጹም የሆነ ህይወትን በመኖር፣ የህይወቱን የተቀደሰ አላማን በማክበር የእግዚአብሔርን ፍቅር አሳይቷል። ኩራተኛም አልነበረም። በኩራት እራሱን አነፋፍቶም አልነበረምም። በምንም ታማኝ ያልነበረበትም የለም። ሁል ጊዜም ትሁት ነበር። ሁልጊዜም ልባዊ ነበር። ሁልጊዜም ታዛዥ ነበር።

በታዋቂ አታላዩ፣ እንዲሁን ዲያብሎስ፣ እንዲፈተን በመንፈስ ወደ ዱር ቢመራም፣ እንዲሁም በዲያብሎስ፣ ቢፈተንም፤ ለ40 ቀን እና ለ40 ምሽት በመጾም በሰውነቱ ደካማ ቢሆንም እና "ቢራብም"፤ ግን ክፉው ኢየሱስን የሚያታልሉ እና የሚፈትኑ ቢያቀር ብለትም፣ ትክክል እንደሆነ ከሚያውቀው ዞር ለማለት እምቢ በማለት የመለኮታዊ ታዛዥነት ምሳሌ ሰጠን።[13]

ስቃዩ እንዲህ ሆኖ "ላቡ ወደምድር የሚ ንጠባጠቡ ደሞች የነበሩትን"[14] የሚፅናናበት የገትሰመኒ ስቃይ ሲመጣበትም፣ ታዛዥ ልጅን እንድዚህ በማለት ምሳሌ አሳየ፣ "ብትፈቅድ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ እያለ ይጸልይ ነበር።"[15]

አዳኝ የመጀመሪያ ሐዋሪያቱን እንዳስተ ማረው፣ እኔን እና እናንተን "ተከተሉኝ"14 በማለት ያስተምራል። [16]ለመታዘዝ ፈቃደኞች ነን?

የምንፈልጋቸው እውቀቶች፣ ለም ንንጓጓቸው መልሶች፣ እናም የሚ ቀየረው አለም ፈተናዎችን ለመቋቋም የምንፈልጋቸውጥንካሬን የእኛ ለመሆን የሚ ችሉት የጌታን ትእዛዛት በፈቃደኛነት ስናከብር ስንታዛዝባቸው ነው። የጌታን ቃላት እንደገናም እጠቅሳለሁ፥ "[የእግዚአብሔርን ትእዛዛት] የሚያከብርም፣ በእውነት እና ሁሉንም ነገሮች በማወቅ እስከሚከበር ድረስ፣ እውነት እና ብርሀንን ይቀበላል።"[17]

ለታዛዦቹ ቃል ለተገባው ብዙ ስልማቶች እንድንባረክ ትሁት ጸሎቴ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ፣ በጌታችንና በአዳኛችን ስም፣ አሜን።

ማስታወሻዎች

1. "አቤቱ፣ እውነት ምንድን ነው?" *Hymns*, no. 272።
2. ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች 93፥24፣ 26–28
3. 1 ሳሙኤል 15፥22
4. ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች 64፥34
5. 1 ኔፊ 3፥7
6. ዘፍጥረት 22፥12
7. ዘፍጥረት 22፥18
8. ጆሴፍ ኤፍ. ስሚዝ, "Discourse፣" *Deseret News፣* ህዳር 12፣ 1873፣ 644።
9. ጎርደን ቢ. ሒንክለይ፣ "If Ye Be Willing and Obedient፣" *Ensign፣* Dec. 1971፣ 125
10. Abraham 3፥25
11. ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች 132፥5
12. ዕብራውያን 5፥8
13. ማቴዎስ 4፥1–11
14. ሉቃስ 22፥27
15. ሉቃስ 22፥42
16. ዮሀንስ 21፥22
17. ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች 93፥28

# ለጊዜአችን ትምህርቶች

የመልከጸዴቅ ክህነትና የሴቶች መረዳጃ ማህበር የአራተኛው እሁዶች ትም ህርቶች "ለጊዜአችን ትምህርቶች" የተወከሉ ይሆናሉ። እያንዳንድ ትምህር ትም በቅርብ ከነበረው የአጠቃላይ ጉባኤ አንድ ወይም ተጨማሪ ንግግሮች መምረጥ ይቻላል። የካስማ እና የአውራጃ መሪዎች የትኛዎቹ ንግግሮች መጠቀም እንደሚ ገባቸው መምረጥ ይችላሉ፣ ወይም ይህን ሀላፊነት ለኤጲስ ቆጶስ እና ለቅርንጫፍ መሪ ለመስጠት ይችላሉ። የመልከጼደቅ የክህነት ስልጣን ወንድሞች እና የሴቶች መረዳጃ ማህበር እህቶች አንድ አይነት ንግ ግሮችን በአንድ እሁድ ቀን ማጥናታቸው አስፈላጊነትን መሪዎች ደጋግመው ማሳሰብ ይገባቸዋል።

በአራተኛው ሰንበት ትምህርት ተሳታፊ ዎች የቅርቡን የአጠቃላይ ጉባኤ መጽሄት እንዲያጠኑ እና ወደ ክፍል እንዲያመጡ ይበረታቱ።

**ከንግግሮች ትምህርትን የማዘጋጃ ሀሳቦች**

ንግግሮችን ስታጠኑ እና ስታስተምሩ መንፈስ ቅዱስ ከእናንተ ጋር እንዲሆን ጸልዩ። ሌሎች መፅሀፎችን በመጠቀም ትምህርትን ለማዘጋጀት ሀሳብ ይመጣላችሁ ይሆናል፣ ነገር ግን የጉባኤ ንግግሮች የትም ህርት መረጃ እንዲሆን ፈቃድ የተሰጠበት ነው። የተመደባችሁትም በቤተክርስትያና የቅርብ አጠቃላይ ጉባኤ ውስጥ የተሰጡትን ትምህርቶች ሌሎችን ወንጌሉን ለመኖር እና ለመማር እንድትረዱአቸው ነው።

የክፍል አባሎች ፍላጎትን የሚያሟሉ መሰረታዊ መርሆችን እና ትምህርቶችን በመፈለግ ንግግሮችን አጥኑ። ደግሞም ታሪኮችን፣ ቅዱስ መጻህፍት የተጠቀሱብ ትን፣ እና እነዚህን እውነቶች ለማስተማር የሚረዷችሁን ቃላቶች ፈልጉ።


መሰረታዊ መርሆችን እና ትምህርቶችን እንዴት እንደምታስተምሩም ዘርዝራችሁ ጻፉ። የክፍል አባላትን የሚረዱ ጥያቄዎችን አስቡባቸው።

- በንግግሮች ውስጥ መሰረታዊ መርሆችን እና ትምህርቶችን ፈልጉ።
- ስለትርጉማቸው አስቡበት።
- መረዳትን፣ ሀሳባቸውን፣ አጋጣሚያቸ ውን፣ እና ምስክሮችን አካፈሉ።
- እነዚህን መሰረታዊ መርሆች እና ትምህ ርቶች በህይወታቸው ይጠቀሙባቸው።

| ትምህርቶቹ የሚማሩበት ወራት | የአራተኛው እሁድ የትምህርት መርጃዎች |
|---|---|
| ሚያዝያ 2012 (እ.አ.አ)–ጥቅምት 2012 (እ.አ.አ) | በሚያዝያ 2013 (እ.አ.አ) አጠቃላይ ጉባኤ የተሰጠ ንግግር * |
| ጥቅምት 2012 (እ.አ.አ)–ሚያዝያ 2013 (እ.አ.አ) | በጥቅምት 2012 (እ.አ.አ) አጠቃላይ ጉባኤ የተሰጠ ንግግር * |

** ለሚያዝያ እና ለጥቅምት የአራተኛ ሰንበት ትምህርቶች፣ ወደፊት ከነበሩት ወይም በቅርብ ከነበሩት የጉባኤ ንግግሮች መምረጥ ይቻላል። እነዚህ ንግግሮች (በብዙ ቋንቋዎች) በ* conference.lds.org conference.lds.org*ውስጥ ይገኛሉ።*

© 2013 Intellectual Reserve, Inc.መብቶቹ በህግ የተጠበቁ። በዩ.ኤስ.ኤ የታተመ። እንግሊዘኛ የተፈቀደበት፥ 6/12 (እ.አ.አ) ትርጉም የተፈቀደበት፥ 6/12 (እ.አ.አ)
*First Presidency Message, May 2013.* Amharic. 10665 506 ትርጉም



**በፕሬዘደንት ሔንሪ ቢ አይሪንግ**
*የቀዳሚ አመራር የመጀመሪያ አማካሪ*

# “ወደ እኔ ኑ”

*በቃላቶቹ እና በምሳሌው፣ ወደ እሱ እንዴት መቅረብ እንደምንችል ክርስቶስ አሳይቶናል።*

በዚህ በኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርሰቲን ጉባኤ ከእናንተ ጋር በመሆኔ አመስጋኝ ነኝ። ይህች የእ ርሱ ቤተክርስቲያን ናት ወደ መንግስቱ ስንገባ ስሙን በእራሳችን ላይ እንቀበላለን። እርሱ እግዚአብሔር፣ ፈጣሪ፣ እና ፍጹም ነው። እኛ ለሞት እና ለኃጢያት ተገዢ የሆንን ሟቾች ነን። ነገር ግን ለእኛና ለቤተሰቦቻችን ባለው ፍቅር፣ ወደ እርሱ እንድንቀርብ ይጋብዘናል። ቃላቱም እንዲህ ይላሉ፥ “ወደ እኔ ቅረቡ እና እኔም ወደ እናንተ እቀርባለሁ፤ ተግታችሁም ፈልጉኝ እናም ታገኙኝማላችሁ፤ ለምኑ፣ ትቀበላላችሁ፤ አንኳኩ፣ ይከፈትላችሁማል።”[1]

በዚህ በትንሳኤ ጊዜ እርሱን ለምን እንደምናፈቅር እና ታማኝ ደቀ መዛሙርቶቹን የልብ ጓደኞቹ እንደሚያደግር ስለገባው ቃል ኪዳን እንድናስታውስ ተደርገናል። አዳኝ ያን ቃል ኪዳን ገብቷል እናም ለእርሱ በምናገለግልበት እርሱ እንዴት ወደ እኛ እንደሚመጣ ነግሮናል። አንዱ ምሳሌም ኦሊቨር ካውደሪ በመፅሐፈ ሞርሞን ትርጉም ከነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ጋር ጌታን ሲያገለግል በተሰጠው ራዕይ ነበር፥ “እነሆ፣ አንተ ኦሊቨር ነህ፣ እናም በፈቃድህ ምክንያት ተናግሬሀለሁ፤ ስለዚህ እነዚህን ቃላት በልብህ አከማች። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመጠበቅ ታማኝ እና ትጉህ ሁን፣ እናም በፍቅሬ እቅፍ ውስጥም አደርግሀለሁ።”[2]

በብዙ ጊዜ ለትእዛዛት ታዛዥነት በመሆን ወደ ጌታ የመቅረብ እና እርሱም ወደ እኔ የመቅረቡን ደስታ አገኝቻለሁ።

እናንተም እንደዚህ አይነት አጋጣሚዎች አላችሁ። ይህም በቅዱስ ቁርባን ስብሰባ ለመሳተፍ ስትመርጡ ይሆናል። በልጅነቴበሰንበት ላይ ይህም ለእኔ ደረሰ። በእነዚያ ቀናት ቅዱስ ቁርባንን የምንቀበለው በምሽት ስብሰባ ጊዜ ነበር። ከቤተሰቤና ከቅዱሳን ጋር ለመሰብሰብ ትእዛዝን ሳከብር የነበረበኝ ከ65 አመት በፊት የነበረኝ የአንድ ቀን ትዝታ አሁንም ወደ ጌታ እንድቀርብ ያደርገኛል።

በውጪ ጭለማና ብርድ ነበር። ከወላጆቼ ጋር በቤተክርስቲያን ውስጥ እያለሁ ብርሀን እና ሙቀት ተሰምቶኝ እንደነበር አስታውሳለሁ። ከሰማይ አባታችን ጋር ልጁን ሁልጊዜ ለማስታወስ እና ትእዛዛቱንለማክበር ቃል ኪዳን እየገባን በአሮናዊ ክህነት ባለስልጣኖች የተላለፉትን ቅዱስ ቁርባን ወሰድን።

በስብሰባው መጨረሻ ላይ “Abide with Me ፤ ’Tis Eventide” የሚለውን መዝሙር ዘመርን፣ በዚህም “አቤቱ አዳኝ፣ በምሽት ከእኔ ጋር ቆይ” የሚሉ ቃላት ነበሩ።[3]

በዚያ ምሽት የአዳኝ ፍቅር እና ቅርብነት ተሰማኝ። እናም የመንፈስ ቅዱስ መፅናኛም ተሰማኝ።

በልጅነቴት በዚያ የቅዱስ ቁርባን ስብሰባ የተሰማኝን የአዳኝ ፍቅር እና የእርሱ ቅርብ ነትን ስሜት እንደገና ለማግኘት ፈለግሁኝ። ስለዚህ በቅርብ ሌላ ትእዛዝን አከበርኩኝ። ቅዱሳት መጻህፍትን ፈተሸኩኝ። በእነዚህም ውስጥ፣ መንፈስ ቅዱስ ከሞት የተነሳው ጌታ ሁለት ሐዋሪሪያት ወደ ቤታቸው እንዲመጣና ከእነርሱ ጋር እንዲቆይ የጠየቁበትን ግብዣ ሲቀበል የተሰማቸው አይነት ስሜት ለማግኘት እንደገና ለመመለው እንደምችል አወቅሁኝ።

ከተሰቀለበት እና ከተቀበረበት ሶስተኛ ቀን በኋላ ስለነበረው አነብባለሁ። ታማኝ ሴቶች እና ሌሎች ከመቃብሩ ድንጋዩ ተንከባሎ አገኙት እናም ሰውነቱ በዚያ አልነበረም። ለእርሱ ባላቸው ፍቅር ምክንያት ሰውነቱን ለመቀባት ነበር የመጡት።

ሁለት መላእክት መጡ እና እንዲህ በማለት ለምን እንደሚፈሩ ጠየቋቸው፥

“ሕያውን ከሙታን መካከል ስለ ምን ትፈልጋላችሁ?

“ተነሥቶአል እንጂ በዚህ የለም። የሰው ልጅ በኃጢአተኞች እጅ አልፎ ሊሰጥና ሊሰቀል በሦስተኛውም ቀን ሊነሣ ግድ ነው እያለ ገና በገሊላ ሳለ ለእናንተ እንደ ተናገረ አስቡ።”[4]

የማርቆስ ወንጌል ከመላእክት አንዱ የሰጠውን መመሪያ ጨምሯል፥ “ነገር ግን ሄዳችሁ ለደቀ መዛሙርቱ ለጴጥሮስም። ወደ ገሊላ ይቀድማችኋል፤ እንደ ነገራችሁ በዚያ ታዩታላችሁ ብላችሁ ንገሩአቸው አላቸው።”[5]

ሐዋሪያት እና ደቀ መዛሙርቶች በኢየሩሳሌም ተሰብስበው ነበር። ልንሆን እንደምንችልም፣ እነርሱ ስለሙት እና ስለትንሳኤው የሰሙት ሀተታ ምን ትርጉም እንዳለው ሲነጋገሩ ፈርተውና ተደንቀው ነበር።

በዚያ ቀን ከሰዓት በኋላ ሁለቱ ሐዋሪያት ከኢየሩሳሌም ወደ ኤማሁስ በሚመራው መንገድ ላይ ነበሩ። በትንሳኤ የተነሳው ክርስቶስ በመንገዱ መጣላቸው እና ከእነርሱ ጋር ይሄድ ነበር። ጌታ ወደ እነርሱ መጥቶ ነበር።

የሉቃስ መፅሐፍ ከእነርሱ ጋር አብረን እንድንሄድ ያደርጋል፥

“ሲነጋገሩና ሲመራመሩም፥ ኢየሱስ ራሱ ቀርቦ ከእነርሱ ጋር ይሄድ ነበር፤

“ነገር ግን እንዳያውቁት ዓይናቸው ተይዞ ነበር።

“እርሱም። እየጠወለጋችሁ ስትሄዱ፥ እርስ በርሳችሁ የምትነጋገሩአቸው እነዚህ ነገሮች ምንድር ናቸው? አላቸው።

“ቀለዮጳ የሚባልም አንዱ መልሶ። አንተ በኢየሩሳሌም እንግዳ ሆነህ ለብቻህ ትኖራለህን? በእነዚህ ቀኖች በዚያ የሆነውን ነገር

አታውቅምን? አለው።”[6]

የእስራኤል አዳኝ እንደሆነ በእርሱ እምነት ስለነበራቸው ኢየሱስ ሞት ስላላቸው ሀዘን ነገሩት።

በሀዘን ላይ ላሉት እነዚህ ሁለት ሀዘነኛ ደቀመዝሙርቶች ሲናገር ከሞት በተነሳው ጌታ ድምጽ ውስጥ የፍቅር ስሜት ይሰማ ይሆንም ነበር።

“እርሱም፣ እናንተ የማታስተውሉ፥ ነቢያትም የተናገሩትን ሁሉ ልባችሁ ከማመን የዘገየ፤

“ክርስቶስ ይህን መከራ ይቀበል ዘንድና ወደ ክብሩ ይገባ ዘንድ ይገባው የለምን? አላቸው።

“ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ ስለ እርሱ በመጻሕፍት ሁሉ የተጻፈውን ተረጐመላቸው።”[7]

ከዚያም ከትንሽ ልጅነቴ ጊዜ ጀምሮ ልቤት ያሞቅ የነበረው ጊዜ መጣ፥

“ወደሚሄዱበትም መንደር ቀረቡ፥ እርሱም ሩቅ የሚሄድ መሰላቸው።

“እነርሱ፣ ከእኛ ጋር እደር፥ ማታ ቀርቦ አልና ቀኑም ሊመሽ ጀምሮአል ብለው ግድ አሉት፤ ከእነርሱም ጋር ሊያድር ገባ።[8]

ኤማሁስ ደንበር አቅራቢያ ወዳለው ወደ ደቀመዛሙርቶቹ ቤት ለመግባት አዳኝ በዚያ ምሽት ግብዣን ተቀበለ።

ለመመገብ ከእነርሱ ጋር ተቀመጠ። እንጀራውን አንስቶ ባረከ፣ ቆርሶም ሰጣቸው። ዓይናቸውም ተከፈተ፥ አወቁትም። ከዚያም እርሱም ከእነርሱ ተሰወረ። ሉቃስ የእነዚያ የተባረኩ ደቀመዛሙርቶች ስሜት ለእኛ መዝግቦልን ነበር፥ “እርስ በርሳቸውም፣ በመንገድ ሲናገረን መጻሕፍትንም ሲከፍትልን ልባችን ይቃጠልብን አልነበረምን?” ተባባሉ።[9]

በዚያም ሰዓት፣ ሁለቱ ሐዋሪያት ምን እንደደረሰባቸው ለአስራ አንዱ ሐዋሪያት ለመንገር ወደ ኢየሩሳሌም በፍጥነት ሄዱ። በዚያም ጊዜ አዳኝ እንደገና ታየ።

ለአባቱ ልጆች ኃጢያቶች በሙሉ ለመክፈል እና የሞትን እስር ለመበጠስ ስለተተነበየበት ተልዕኮው ገመገመ።

“እንዲህም አላቸው። ክርስቶስ መከራ ይቀበላል በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል፥

“በስሙም ንስሐና የኃጢአት ስርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል ተብሎ እንዲሁ ተጽፎአል።

“እናንተም ለዚህ ምስክሮች ናችሁ።”[10]

የአዳኝ ቃላት በዚያ ጊዜ ለደቀመዛሙርቶቹ እንደነበሩ አሁንም ለእኛ እውነት ናቸው። ስለእነዚህ ነገሮች ምስክሮች ነን። ወደ ኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን በምንጠመቅበት ጊዜ የተቀበልናቸው ግርማዊ ሀላፊነቶች ከብዙ መቶ አመቶች በፊት በሞርሞን ውሀዎች ላይ ነቢዩ አልማ ግልፅ አድርጎልን ነበር፥

“እናም እንዲህ ሆነ እንዲህም አላቸው፥ እነሆ፣ የሞርሞን ውሃ ይህ ነው፣ (እንደዚህም ነበር የተጠሩት) እናም አሁን፣ እናንተ ወደ እግዚአብሔር በረት ለመምጣትና፣ ህዝቡ ትባሉ ዘንድ፣ እንዲሁም አንዳችሁ የአንዳችሁን ሸክም ቀላል እንዲሆኑ ዘንድ ለመሸከም ፈቃደኞች በመሆን እንደፈለጋችሁ፤

አዎን፣ እናም ከሚያዝኑት ጋር ለማዘን፤ መፅናናትን ለሚፈልጉም ካፅናናችኋቸው፤ እናም በሁሉም ጊዜ በሁሉም ነገርና፣ በምትኖሩበት ቦታዎች ሁሉ፣ እስከሞት ድረስ፣ የእግዚአብሔር ምስክር በመሆን ትቆሙ ዘንድና፣ በጌታ ትድኑ ዘንድ፣ እናም ዘለዓለማዊ ህይወትም ይኖራችሁ ዘንድና የፊተኛውን ትንሳኤ ከሚያገኙት ጋርም ለመቆጠር ፈቃደኞች ከሆናችሁ —

አሁን እላችኋለሁ፣ ይህ የልባችሁ ፍላጎት ከሆነ፣ እርሱን እንደምታገለግሉ እናም ትዕዛዛቱን እንደምትጠብቁ፣ እርሱም በእናንተ ላይ መንፈሱን በብዛት ያፈስባችሁ ዘንድ በፊቱ እንደምስክርነት ከእርሱ ጋር ቃል ኪዳን በመግባት በጌታ ስም ለመጠመቅ የሚያስቸግራችሁ ምንድን ነው?

“እናም አሁን ህዝቡ ይህንን አባባሉን በሰሙ ጊዜ፣ በደስታ አጨበጨቡ፣ እናም በደስታ ይህ የልባችን ፍላጎት ነው ብለው ጮኹ።”[11]

እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ከፍ ለማድረግ እና በህይወት እስካለን ድረስ የአዳኝ ምስክር ለመሆን በቃል ኪዳን ስር ነን።

ይህን ያላውድቀት ለማድረግ የምንችለው ለአዳኝ ስላለን ፍቅር እና እርሱ ለእኛ ስላለን ቅፍር ስሜት ሲኖረን ብቻ ነው። ቃል ለገባናቸው ታማኝ ስንሆን፣ ለእርሱ ያለን ፍቅር ይሰማናል። እርሱን በማገልገል ሀይሉና ወደ እርሱ የምንቀርብበት ስለሚሰማን ይህም ይጨምራል።

ፕሬዘደንት ቶማስ ኤስ. ሞንሰን ጌታ ለታማኝ ደቀመዛሙርቶቹ ጌታ ስለገባው ቃል ኪዳን በየጊዜው እንድናስታውስ ያደርጉናል፥ “እናም የሚቀበሏችሁም ቢሆን፣ እኔም በዚያም እገኛለሁ፣ በፊታችሁም እሄዳለሁና። በቀኛችሁ እና በግራችሁ እሆናለሁ፣ እናም መንፈሴም በልቦቻችሁ ውስጥ ይገኛል፣ እናም መላእክቶቼም እንዲያዝሏችሁ ይከብቧችኋል።”[12]

እኔ እና እናንተ እርሱ ወደ እኛ ሲቀርብ ስሜት የምናገኝበት ሌላ መንገድ አለ። በእርሱ አገልግሎት መለኮታዊ ስንሆን፣ በቤተሰቦቻችን ለምናፈቅራቸው የቀረበ ይሆናል። ለጌታ አገልግሎት ወደ ሌላ ቦታ እንድሄድ ወይም ቤተሰቤን ትቼ እንድሄድ በምጠራበት በእያንዳንዱ ጊዜ፣ ጌታ ባለቤቴን እና ልጆቼን እንደሚባርክ ተመልክቻለሁ። የእርሱን አፍቃሪ አገልጋዮችን እና ቤተሰቤት ወደ እርሱ የሚያቀርቡ እድሎችን ያዘጋጃል።

እንዲህ አይነት በረከቶችንም በህይወታችሁ ተሰምቷችኋል። ብዙዎቻችሁ ከዘለአለም ህይወት መንገድ ተንከራተተው የሚሄዱ የምናፈቅራቸው አሉ። እነርሱን ለመመለስ ምን በተጨማሪ ለማድረግ እንደምትችሉ ታስቡበትም ይሆናል። እርሱን በእምነት ስታገለግሉ ጌታ ወደ እነርሱ እንዲቀርብ ልትመኩበት ትችላላችሁ።

ጆሴፍ ስሚዝ እና ኦሊቨር ካውደሪ ከቤተሰቦቻቸው በተለዩበት ጊዜ ጌታ የገባላቸውን ቃል ኪዳን ታስታውሳላችሁ፥ “በእውነት ባልንጀሮቼ ስድኒ እና ጆሴፍ፣ ጌታ ለእናንተ እንዲህ ይላል፣ ቤተሰቦቻችሁ ደህና ናቸው፤ በእጆቼም ውስጥ ናቸው፣ እና መልካም እንደሚመስለኝም አደርግባቸዋለሁ በእኔ ሁሉም ሀይል አለና።”[13]

እንደ አልማ እና እንደ ንጉስ ሞዛያ፣ አንዳንድ ታማኝ ወላጆች ጌታን በደንብ እና ለረጅም ጊዜ ቢያገለግሉም፣ ምንም እንኳን ወላጆቻቸው ለጌታ ወስዋዕት ቢያደርጉም የተንከራተቱ ልጆች ነበሯቸው። በሚያፈቅሩ እና በታማኝ ጓደኞች ቢረዱም፣ ለማድረግ የሚችሉትን ሁሉ ምንም ውጤት ያለማየት እድርገዋል።

አልማ እና የዚያ ቀኑ ቅዱሳን ለልጁና ለንጉስ ሞዛያ ልጆች ይጸልዩ ነበር። መልአክም መጣ። የእናንተ ጸሎት እና እምነታቸውን የሚጠቀሙበት ሰዎች ጸሎቶች የቤተሰብ አባላትን ለመርዳት የጌታ አገልጋዮችን ያመጣል። ቤተሰብን በዚህ ህይወት እና በዘለአለምየማ ጥፋት አላማ ባለው ሰይጣንና በሚከተሉት ቢጠቁም፣ እነርሱም ወደ ቤት ወደ እግዚአብሔር የሚሄዱበትን መንገድ እንዲመርጡም ይረዳሉ።

በአመጻቸው መልአኩ ለታናሹ አልማ እና ለሞዛያ ወንድ ልጆች የተናገራቸውን ቃላት ታስታውሳላችሁ፥ “እናም በድጋሚ፣ መልአኩ አለ፥ እነሆ፣ ጌታ የዚህን ህዝብ ፀሎት፣ እናም ደግሞ የአባትህን የአልማን ፀሎት ሰምቷል። አንተ ወደ እውነት እውቀትም ትመጣ ዘንድ አንተን በተመለከተ በታላቅ እምነት ፀልዮአል፤ ስለዚህ፣ ለዚህ ዓላማ የእግዚአብሔርን ኃይልና ስልጣን ለማሳመን፣ በእምነታቸው መሰረተ የአገልጋዮቹ ለፀሎት መልስ ያገኝ ዘንድ ነው የመጣሁት።”[14]

እናንተ ለምትጸልዩትና ጌታን ለምታገለግሉት ቃል የምገባላችሁ ለራሳችሁና ለቤተሰቦቻችሁ ለማግኘት የምትመኙትን እያንዳንዱን በረከቶች ታገኛላችሁ ለማለት አይደለም።

ነገር ግን አዳኝ ወደ እናንተ እንደሚቀርብ እና እናንተንና ቤተሰቦቻችሁ ጠቃሚ በሚሆን እንደሚባርካችሁ ቃል ልገባላችሁ እችላለሁ። የእርሱ ፍቅር መፅናኛ እና ሌሎችን ለማገልገል እጆቻችሁ ስትዘረጉ እርሱ ወደ እናንተ የሚቀርብበትን መልስ ሊሰማችሁ ትችላላችሁ። እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ቁስሎች ስትጠግኑ እና በኃጢያት ስር በሀዘን ላይ ያሉትን በኃጢያት ክፍያ መጸዳትን ስታቀርቡላቸው፣ የጌታ ሀይል ይደግፋችኋል። ከእናንተ ጋር ለመርዳት እና ከቤተሰባችሁ በተጨማሪ የሰማይ አባታችንን ልጆች ለመባረክ እጆቹ ተዘርግተዋል።

በክብር ወደ ቤት መመለሻም ተዘጋጅቶልናል። ከዚያም ያፈቀርነው ጌታ ቃል ኪዳን ሲሟላ እንመለከታለን። ከእርሱ እና ከሰማይ አባታችን ጋር ወደምንኖርበት ወደ ዘለአለም ህይወት የሚቀበለንም እርሱ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ይህን እንደዚህ ገልጾታል።

“ፅዮንን ወደፊት ለማምጣት እና ለመመስረት ፈልግ። በነገሮች ሁሉ ትእዛዛቴን ጠብቅ።

“እናም፣ ትእዛዛቴን ብትጠብቅ እናም እስከመጨረሻው ብትጸና ከእግዚአብሔር ስጦታዎች ሁሉ ታላቅ ስጦታ የሆነውን ዘለአለማዊ ህይወት ይኖርሀል።”[15]

“በህይወት ያሉት ምድርን ይወርሳሉ፣ እና የሞቱትም ከሁሉም ድካሞቻቸው ያርፋሉ፣ እናም ስራዎቻቸው ይከተሏቸዋል፤ እናም ባዘጋጀሁላቸው በአባቴም ቤቶች ውስጥ አክሊልን ይቀበላሉ።”[16]

በመንፈስ እንዲህ የሚለውን የሰማይ አባትን ግብዣ ለመከተል እንደምንችል እመሰክራለሁ፥ “ይህ ውድ ልጄ ነው። አድምጠው!”[17]

በእርሱ ቃላት እና በምሳሌው፣ ክርስቶስ ወደ እርሱ እንዴት ለመቅረብ እንደምንችል አሳይቶናል። በጥምቀት በር ወደ ቤተክርስቲያኑ ለመግባት የሚመርጠው እያንዳንዱ የሰማይ አባት ልጅ በዚህ ህይወት ወንጌሉን ለመማር እና “ወደ እኔ ኑ” የሚለውን ግብዣ ከተጠሩት አገልጋዮቹ ለመስማት እድል ይኖረዋል።[18]

በምድር ባለው በመንግስቱ ውስጥ እና በመንፈስ አለም ውስጥ የእርሱ የቃል ኪዳን አገ፤ ጋይ የሆነ እያንዳንዱም ለእርሱ ሌሎችን ሲባርኩና ሲያገለግሉ በመንፈስ የእርሱን መመሪያ ይቀበላሉ። የእርሱ ፍቅር እና ደስታ ስሜትም ወደ እርሱ በመቅረብ ይሰማቸዋል።

በኤማሁስ መንገድ በነበረ ቤት ውስጥ ከነበሩት ሁለቱ ደቀመዛሙርቶች ጋር አብሬ እንደነበርኩኝ ያህል በትንሳኤ ለተነሳው ጌታ ምስክር ነኝ። በፓልማይራ ጥሻ ውስጥ በአስደናቂው ጠዋት ብርሀን ውስጥ ጆሴፍ ስሚዝ አብንና ወልድን በማየት እንዳለው እውቀት እኔም እርሱ ህያው እንደሆነ አውቃለሁ።

ይህችም የኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ ቤተክርስቲያን ናት። በፕሬዘደንትቶማስ ኤስ. ሞንሰን በተያዘው የክህነት ስልጣን ብቻ ነው እንደ ቤተሰብ ተሳስረን ከሰማይ አባታችንና ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ለመኖር የምንችለው። በፍርድ ቀን በአዳኝ ፊት፣ ፊት ለፊት እንቆማለን። ይህም በዚህ ህይወት እርሱን በማገልገል ወደ እርሱ ለቀረቡት የደስታ ጊዜ ይሆናል። “መልካም፥ አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ” የሚሉትን ቃላት ማድመጥም ያስደስታል። ስለዚህ በትንሳኤ ስለተነሳው አዳኝ እና ቤዛችን እንደ ምስክርነት የምመሰክረው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው፣ አሜን።

ማስታወሻዎች

1. ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች 88፥63
2. ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች 6፥20
3. “Abide with Me; ’Tis Eventide,” *Hymns*, no. 165።
4. ሉቃስ 24፥5–7
5. ማርቆስ 16፥7
6. ሉቃስ 24፥15–18
7. ሉቃስ 24፥25–27
8. ሉቃስ 24፥28–29
9. ሉቃስ 24፥32
10. ሉቃስ 24፥46–48
11. ሞዛያ 18፥8–11
12. ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች 84፥88
13. ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች 100፥1
14. ሞዛያ 27፥14
15. ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች 14፥6–7
16. ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች 59፥2
17. ጆሴፍ ስሚዝ ታሪክ 1፥17)።
18. ማቴዎስ 11፥28
19. ማቴዎስ 25:21

© 2013 by Intellectual Reserve, Inc. መብቶቹ በህግ የተጠበቁ። በዩ.ኤስ.ኤ የታተመ። እንግሊዘኛ የተፈቀደበት፥ 6/12 (እ.አ.አ) ትርጉም የተፈቀደበት፥ 6/12 (እ.አ.አ)
*Visiting Teaching Message, May 2013.* Amharic. 10665 506 ትርጉም